# የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

## የመስከረም **2014** ዓ.ም ምርጫ የቅድመ ምርጫ ትዝብት ሪፖርት

*መስከረም 18 ቀን 2014 ዓም*
አዲስ አበባ

*መግቢያ*

ካለፈው መጋቢት 2013 ጀምሮ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ ከስድስተኛው አገራዊ ምርጫ ጋር የተያያዙ በርካታ እንቅስቃሴዎችን፤ የመራጮችን ምዝገባ እና ድህረ ምርጫ ከባቢን እንዲሁም ሰኔ 14/2013 የተካሄደውን የድምጽ መስጫ ቀን ሲታዘብ ቆይቷል። በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች በሰኔ 14/2013 በተካሔደው አገራዊ ምርጫ ላይ ያለመሳተፋቸውን ታሳቢ በማድረግ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መስከረም 20/2014 ሁለተኛው የድምጽ መስጫ ቀን እንዲሆን መወሰኑም ይታወሳል። ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ 41 የሚሆኑ የረጅም ጊዜ ታዛቢዎችን በመመልመል እና በማሰልጠን የቅድመ ምርጫ ሁኔታን ለመገምገም ምርጫ ባልተካሔደባቸው የምርጫ ክልሎች (በሐረሪ ክልል፣ ሱማሌ ክልል፣ በቤንሻንጉል ክልል የተወሰኑ አካባቢዎች ፣ በአማራ ክልል እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል) አካባቢዎች አሰማርቷል ። ይሁን እንጂ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በጸጥታ ችግር በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች ምርጫ እንደማይካሄድ ማሳወቁን ተከትሎ ኅብረቱ የቅድመ ምርጫ ትኩረቱን ወደ ሐረሪ፣ ሱማሌ እና ደቡብ ክል|ሎች አድርጓል፤ ይህም በሪፖርቱ ላይ ተንጸባርቋል።

ከነሐሴ 4/2013 ዓም  ጀምሮ የኅብረቱ የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች የመራጮች ትምህርት እና መረጃን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የምረጡኝ ቅስቀሳ፣ ልዩ ትኩረት የሚያሻቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች (ወጣቶችን፣ ሴቶችን፣ እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን) እንቅስቃሴ፣ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ግጭቶችን እና የጥላቻ ንግግሮችን እንዲሁም ግጭት ቀስቃሽ ቋንቋዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ሲታዘቡ ቆይተዋል። የኅብረቱ ታዛቢዎች ማንኛውንም አይነት አሳሳቢ ሁኔታዎችን ሲመለከቱ ወይም ሲሰሙ በአስቸኳይ ሪፖርት እንዲያደርጉም ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።

የኅብረቱ የመረጃ ማዕከል ከነሐሴ 4 እስከ ጳጉሜ 4/2013 ዓም ድረስ ምርጫ ይካሄድባቸዋል ብሎ ባሰበባቸው ክልሎች ማለትም በሐረሪ ክልል፣ ሱማሌ ክልል፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተወሰኑ አካባቢዎች ፣ በአማራ ክልል እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ካሰማራቸው ታዛቢዎቹ 279 ሪፖርቶችን ተቀብሏል። ይሁን እንጂ ይህ የመስከረም 20፣ 2014 ዓም የቅድመ ምርጫ ትዝብት ሪፖርት በመስከረም ወር ምርጫ እንዲካሄድ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በወሰነባቸው ክልሎች (በሐረሪ፣ ሱማሌ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል) ከተሰማሩ ታዛቢዎች በተሰበሰቡ 191 ሪፖርቶች ላይ የተመረከዘ ነው። ይህ ሪፖርት ከነሐሴ **4** እስከ ጳጉሜ **4** ቀን **2013** ዓም በሶስቱ ክልሎች በተሰማሩ የህብረቱ ታዛቢዎች ባደረጉት ትዝብት ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው።

የትዝብት ግኝቶች

የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ የቅድመ ምርጫ ትዝብትን በተጠቀሱት ክልሎች ለማካሄድ እንዲያስችለው የሂደቱን ተዓማኒነት እና ግልፀኝነት ለመመዘን የሚረዱ መጠይቅ (Checklist) ተጠቅሟል። በዚህም የምረጡኝ ቅስቀሳ ሒደቶችን ለመታዘብ ያለሙ ጥያቄዎችን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን፣ የመራጮች ትምህርትን፣ ከምርጫው ጋር በተያያዘ በመራጮች ወይም በምርጫ ሰራተኞች ላይ እንዲሁም በሲቪል ማኅበረሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችል ተፅዕኖን ለመታዘብ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ተካተውበታል። ታዛቢዎቹ አሳሳቢ ሁኔታዎችን በተመለከተ መረጃዎችን ከኅብረቱ በተሰጣቸው ቅጽ ላይ በማስፈር

ለህብረቱ ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ በታች የተካተቱት ግኝቶች አስቀድሞ በተጠቀሱት እና ወደ ኅብረቱ በተላኩ የታዛቢዎች ሪፖርቶች ላይ የተመረኮዙ ናቸው።

## ለመስከረም ምርጫ 2014 የምረጡኝ ቅስቀሳ

የምርጫ ቅስቀሳ ከማንኛውም ምርጫ በፊት ያለ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የምርጫ ቅስቀሳ ዜጐች የመምረጥ፣ የመመረጥ፣ እንዲሁም የፖለቲካዊ መብት ማለትም የመደራጀት፣ የመሰብሰብ እንዲሁም ሀሳብን የመግለጽ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ የሚያበረታታ ዋነኛው የምርጫ ክፍል ነው። ይህን በመገንዘብ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ በመስከረም 2014 ዓም ምርጫ ይደረግባቸዋል በተባሉ አካባቢዎች ላይ የተደረጉ የምረጡኝ ቅስቀሳዎችን በምን አይነት አግባብ እንደተካሄዱ ታዝቧል። የምርጫ ቅስቀሳን በተመለከተ አንዱ ግኝት፤ ለትዝብት የተሰማሩ ታዛቢዎች በተገኙባቸው የምርጫ አካባቢዎች 43 በመቶ የሚሆነው ሪፖርት ምንም አይነት የምረጡኝ ቅስቀሳ አለመካሄዱን የሚያሳይ ሲሆን፤ 57 በመቶ የሚሆኑ ታዛቢዎች ደግሞ የምረጡኝ ቅስቀሳው ምንም አይነት የሚዲያ ሽፋን አለማግኘቱን ሪፖርት አድርገዋል።

የተጠቀሰውን ቁጥር ከምርጫ ቅስቀሳ አስፈላጊነት በተለይም ደግሞ ለማንኛውም ምርጫ ግልፀኝነት፣ አሳታፊነት እና ተአማኒነት ካለው አስፈላጊነት አንፃር የመስከረም 2014 ምርጫ ቅስቀሳ ያልተሟላ ያደርገዋል። ይሁን እንጂ የምረጡኝ ቅስቀሳ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ሰላማዊ እና አካታች እንደነበር መግለጽ ይቻላል። ሴቶች እና ወጣቶችን በተመለከተም ቀጣይ ቁጥሮችን እንመለከት።

- የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ ትዝብት ለማድረግ በተንቀሳቀሰባቸው አካባቢዎች ከድምጽ መስጫ ቀን አስቀድሞ የሚካሄደው የምረጡኝ ቅስቀሳን በተመለከተ ውስንነትን አይቷል። ከእነዚህም ውስጥ ለህብረቱ ከደረሱት ሪፖርቶች መካከል 5 በመቶ የሚሆኑት ብቻ የምረጡኝ ቅስቀሳዎች በመንግስት መታገዳቸውን ያስረዳሉ። እነዚህ ሪፖርቶችም የቀረቡት ከሱማሌ ክልል ብቻ ነው።

- አካታችነትን በተመለከተ፤ ህብረቱ በታዘበባቸው አካባቢዎች 67 በመቶ የሚሆኑት የሴቶችን ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩ ነበሩ። በተመሳሳይም 70.91 በመቶ የሚሆኑት የታዛቢዎች ሪፖርቶች የወጣቶችን ተሳትፎም ያማከሉ እንደነበሩ ያሳያሉ። እንዲሁም 60 በመቶ የሚሆነው የታዛቢዎች ሪፖርት ደግሞ ቅስቀሳ በተደረገባቸው አካባቢዎች ላይ የአካል ጉዳተኞችን በምርጫ ሂደት ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ የሚያበረታታ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም፤ የምርጫ ቅስቀሳ ከተካሄደባቸው አካባቢዎች የተገኙ 62.3 በመቶ የሚሆኑ የታዛቢዎች ሪፖርቶች የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ተሳትፎ በቂ እንዳልነበር ያሳዩ ሲሆን፤ በቀጣይም ሊሻሻል እንደሚገባ ገልፀዋል።

- አብዛኛው የታዛቢዎች ሪፖርት (94 በመቶ) እንደሚያስረዳው የምርጫ ቅስቀሳ በሚካሄድበት ወቅት የጸጥታ አካላት ጣልቃ ገብነት አነስተኛ እንደነበር ያመለክታሉ። 95 በመቶ የሚሆነው የታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያሳየው በቅስቀሳ ወቅት ምንም አይነት የጥላቻ ንግግር፣ ሀሰተኛ መረጃ፣ ስድቦች፣ ማስፈራራቶች እና እንግልት አለመኖሩን አሳይተዋል። በቀሪ 5 በመቶ ሪፖርቶች መሠረት ሐሰተኛ መረጃ እንዲሁም እንግልት የተፈፀሙት ሙሉ በሙሉ ከሱማሌ ክልል ነው። በመጨረሻም፤ በምረጡኝ ቅስቀሳ ወቅት 95 በመቶ የታዛቢዎቻችን ሪፖርቶች በሰው ሕይወት ላይ ጉዳት እንዳልደረሰ ቢያስረዱም፤ በቀሪዎቹ 5 በመቶ ሪፖርቶች ላይ በአካል ወይም በንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ያመለክታሉ።

- በመጨረሻም፤ ከተሰበሰበው ሪፖርት ውስጥ 78 በመቶ የሚሆነው የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከል የተቀመጡ ቅደም ተከተሎች አለመተግበራቸውን ያሳያሉ። ይህም በሰኔ ወር በተካሄደው ምርጫ በሽታውን በመከላከል ረገድ የነበሩ ክፍተቶች መባባሳቸውን ያስረዳሉ።

## የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ለመስከረም **2014** የድምጽ አሰጣጥ ያደረገው ዝግጅት

ህብረቱ ከዚህ በታች የተገለፁትን ግኝቶች ይፋ ከማድረጉ በፊት ታዛቢዎቹን ከነሐሴ መጀመሪያ ጀምሮ ምርጫ ይካሄድባቸዋል ተብለው ወደተጠበቁት ክልሎች ያሰማራ ሲሆን፤ ይህም በስተመጨረሻ መስከረም 20፣ 2014 ዓ.ም እንዲደረግ የተወሰነው ምርጫ ጳጉሜ ውስጥ እንደሚደረግ ታሳቢ ተደርጎ ተከናውኗል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ እና የአመራር ውሳኔዎች ከሲቪል ማህበራት የምርጫ ቅስቀሳ፣ የመራጮች ትምህርት እና የምርጫ ትዝብት እንቅስቃሴዎች ላይ ቀጥተኛ እንድምታ እንዳላቸው ይታወቃል። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን በመስከረም 20 ምርጫ የሚያደርገውን ዝግጅት ለመመዘን የሚረዳ መጠይቅ አዘጋጅቷል።

ኅብረቱ ከሀረሪ፣ ከሱማሌ፣ ከደቡብ፣ ከአማራ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ከተቀበላቸው 51 በመቶ ገደማ የሚሆኑ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኩል ያለው ዝግጅት ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለመራጮች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የምርጫ ሂደቱን አመቺ ማድረጉን ያሳያል። ህብረቱ ባሰባሰበው መረጃ መሰረት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል 74 በመቶ እና በአማራ ክልል ደግሞ 79 በመቶ በሚሆኑ ስፍራዎች ላይ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ዝግጅት ለባለድርሻ አካላት (ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የግል እጩ ተወዳዳሪዎች እና ለመራጮች) ምቹ ሁኔታን አለመፍጠሩን ለማወቅ ተችሏል። ይህም ደግሞ ከጠቅላላው አማካኝ ማለትም ከ49 በመቶ ብልጫ ይኖረዋል። ይህም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኩል በቤንሻንጉል እና በአማራ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ምርጫ እንደማይካሔድ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር የሚዛመድ እንድሚሆን ህብረቱ ያምናል። የምርጫ አስፈፃሚዎችን ማሰልጠን ቁልፍ ከሆኑ የቅድመ ምርጫ ዝግጅቶች ውስጥ አንዱ ነው። ወደ ኅብረቱ ደርሰው ከተተነተኑ 171 የታዛቢዎች ሪፖርቶች ውስጥ 64 በመቶው እንደሚያስረዱት ምንም አይነት ስልጠና ለምርጫ አመራሮች ሲሰጥ አለመመልከታቸውን ወይም አለመስማታቸውን ያሳያል። 63 በመቶ የታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚገልጸው ህብረቱ ትዝብት ባደረገበት የግዜ ሰሌዳ ውስጥ የምርጫ ቁሳቁሶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አማካኝነት አለመከፋፈላቸውን ነው።

## የሲቪል ማኅበራት ተሳትፎ፣ የመራጮች እና የምርጫ ሰራተኞ እንግልት እንዲሁም የመራጮች ምዝገባ

የሲቪል ማኅበራት የጎላ ሚና የሚጫወቱበት ሂደት በአንድ ምርጫ ሂደት ላይ ጠቃሚ ግብዓት ነው። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ የሲቪል ማኅበራትን ሚና በቅድመ ምርጫ ከባቢ ሁኔታ ከሲቪል ማኅበራት፣ ከጋዜጠኞች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከባለድርሻ አካላት አንጻር ትዝብት አድርጓል። ኅብረቱ የመራጮች ትምህርትን በተመለከተ የትዝብት መጠይቅ ቅፅ የነበረው ሲሆን፤ ይህም በቅድመ ምርጫ ላይ ላለው የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ቁልፍ ሚና አመላካች ነው። ከዚህ በታች የቀረበው ግኝት በሐረሪ፣ በሱማሌ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች የተካሄዱ የመራጮች ትምህርትን በተመለከተ ከታዛቢዎች በተላኩ ሪፖርቶች ላይ የተመረኮዘ ነው።

- ወደ ኅብረቱ ከደረሱ ሪፖርቶች መካከል ከሱማሌ ክልል ከመጣው ከአንድ ሪፖርት በስተቀር በሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ተሳትፎ ላይ ከመንግስትም ሆነ ከሌሎች አካላት ምንም አይነት ችግር አለመድረሱን ያመላክታል። ይህም አበረታች የሆነ ግኝት ነው። ሆኖም ህብረቱ ይህንን ትዝብት በሚያካሂደበት ወቅት 76 በመቶ የሚሆነው የታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያሳየው ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት በሲቪል

ማህበራት ድርጅቶች በኩል አልተሰጡም። በተመሳሳይ ህብረቱ በሰበሰበው መረጃ መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ ጋዜጠኞች ስራቸውን እንዳይሰሩ ክልከላ እንዳልተደረገባቸው የታወቀ ሲሆን፤ በሱማሌ ክልል በሰባት አጋጣሚዎች ጋዜጠኞች ክልከላ እንደተደረገባቸው እና በአንዱ አጋጣሚ በጋዜጠኞች ላይ ጉዳት መድረሱንም ለማወቅ ተችሏል። በሱማሌ ክልል በዕጩ ተወዳዳሪዎች ላይም ሁለት ጊዜ ጉዳት መድረሱንም የታዛቢዎች ሪፖርቶች ያመላክታሉ።

- በመገናኛ ብዙኃን ተቋማት አማካኝነት የተሰናዱ የመራጮች ትምህርትን በሚመለከት ቁጥራቸው በእጅጉ አናሳ እንደሆነ ታይቷል። ከኅብረቱ የቅድመ ምርጫ ታዛቢዎች ሪፖርት ውስጥ 74 በመቶ የሚሆኑት እንደሚያሳዩት ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት በመንግስታዊም ሆነ በግል፤ እንዲሁም በፌዴራልም ሆነ በክልል የቴሌቪዥን እና ሬዲዮ ጣቢያዎች አማካኝነት አልተሰጠም።
- የኅብረቱ ታዛቢዎች በታዘቡባቸው እና የመራጮች ትምህርት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የጾታ አካታችነት እና ተሳትፎን የሚያበረታቱ እንደነበሩ ከታዛቢዎች በተላኩ በ38.6 በመቶ ሪፖርቶች ውስጥ ታይቷል። በ28 በመቶ ሪፖርቶች ውስጥ የመራጮች ትምህርት የአካል ጉዳተኞችን እኩል ተሳትፎ ሚያበረታታ ሆኖ ተገኝቷል። በሌላ በኩል ደግሞ 39.1 በመቶ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት የመራጮችም ትምህርት በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ መራጮችን ያማከለ ነበር።
- በምርጫ ሂደቱ ላይ የባለ ድርሻ አካላት ላይ (በመራጮች፣ በምርጫ አመራሮች፣ በግል ተወዳዳሪዎች እና በፖለቲካ ፓርቲዎች) ሊደርስ የሚችል ተፅዕኖን በተመለከተ ህብረቱ የታዘበ ሲሆን፤ የተገኙት ሪፖርቶች አዎንታዊ ነበሩ። ወደ ኅብረቱ ከተላኩ ሪፖርቶች ውስጥ 93 በመቶ የሚሆኑት ብሔርን እና ሐይማኖትን መሰረት ያደረጉ እንግልት ወይም ስድብ እንዲሁም የማንኳሰስ አጋጣሚዎች እንዳላጋጠሙ ያሳያሉ።

ምክረ ሀሳብ

በአጠቃላይ ከላይ በተገለፁት ግኝቶች ላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ እንቅስቃሴ እንደ ሌሎች የምርጫ ባለድርሻ አካላት ሁሉ ምርጫዎች የተ እና መቼ እንደሚካሄዱ፤ የቅድመ ምርጫ እና ድኅረ ምርጫ እንቅስቃሴዎች የት እንደሚደረጉ በማወቅ ላይ ይመረኮዛል። ይህ ደግሞ ከቦርዱ ለሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን እና ውሳኔዎችን ማሳወቅን ይጠይቃል። በዚህም የምርጫ ትምህርትን ለመስጠትም ሆነ የመታዘብ እንቅስቃሴን ለማድረግ እጅጉ አስፈላጊ ነው። የኅብረቱ የቅድመ ምርጫ ትዝብት የተጀመረው ምርጫ ቦርድ በድምፅ መስጫ እለት ላይ ካደረገው የማስተላለፍ ውሳኔ በፊት እንደመሆኑ በግኝቱ ላይ ግልፅ ተፅዕኖ እንዳሳረፈበት ያምናል። ይህም ቦርዱ በአንዳንድ ውሳኔዎች ዙርያ በሚወስናቸው ውሳኔዎች ላይ ያለው የመረጃ አሰጣጥ ክፍተት በግልፅ ያሳያል።

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳውን እና ውሳኔዎቹን በተመለከተ አስቀድሞ ማሳወቅ ይኖርበታል። በቤንሻንጉል፣ በአማራ እና ኦሮሚያ ክልል ምርጫ እንደማይካሄድ የተላለፈው ውሳኔ የተገለፀው ዘግይቶ መሆኑ በህብረቱ ስራ ላይ የራሱ ተፅዕኖ አሳድሯል።
- በመራጮች እና በምርጫ ሰራተኞች ላይ የደረሰው እንግልት፣ ከምርጫ ቅስቀሳ ጋር የተያያዙ ክልከላዎች እና ግጭቶች በሱማሌ ክልል ሪፖረት ከተደረገባቸው ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ። ይህም ማለት በድምጽ መስጫ ቀን እና ከዛም ቀጥሎ ባሉት ቀናት ውስጥ ክልሉ ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው መሆኑን ነው። በክልሉ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉ እና የፌዴራል መንግስት አካላት ጋር በመሆን ነጻ፣ ፍትሀዊ እና የተረጋጋ ምርጫን ለማካሄድ እንዲሰራ ይመከራል።
- የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች እና መገናኛ ብዙኃን በመስከረም ወር የመጀመሪያ ሳምንታት በምርጫው ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ጨምረዋል። ቁጥሮች እንደሚያሳዩት የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ውስን እና ዘግይቶ የጀመረ ተሳትፎ በተለይም በመራጮች ትምህርት ላይ መሆኑ አሳሳቢ ነው። የሲቪል ማኅበራትም ያሉትን ውስን እድሎች በመጠቀም ዘላቂ እና በምርጫ ላይ የራሱን አሻራ ለማስቀመጥ እንዲሰራ ይመከራል።

- ኮቪድ 19 አሁንም ተግዳሮት ሆኖ እንደቀጠለ ነው። በምርጫ ቅስቀሳ፣ በመራጮች ትምህርት እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቅድመ ዝግጅት ወቅትም ሪፖረት እንደተደረገው ወረርሽኙን ለመግታት የተቀመጡትን ቅደም ተከተሎች አለመተግበራቸው ታይቷል። ይህ ጉዳይ ህብረቱ በሰኔ 2013 የመራጮች ምዝገባ ትዝብት ሪፖርቱ እንዲስተካከል ምክረ ሃሳብ ያቀረበበት ቢሆንም፤ ችግሩ አሁንም ተባብሶ በመታየቱ ልዩ ትኩረት ያሻዋል።

*መደምደሚያ*

የኢትየጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ በመስከረም 20/2014 ዓ.ም. ለሚካሄደው ምርጫ ከ940 በላይ ታዛቢዎችን በሱማሌ እና ሐረሪ እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የተወሰኑ ስፍራዎች ለማሰማራት ያቀደ ሲሆን፤ ይህም የደቡብ ምዕራብን ሕዝበ ውሳኔ ላይ የሚሳተፉትን ያካትታል። በድምጽ መስጫ ቀን ኅብረቱ ከታዛቢዎቹ የምርጫ ጣቢያዎችን አከፋፈት እና አደረጃጀት፣ የድምጽ አሰጣጡን እና የቆጠራ ሂደቱን የሚመለከቱ ሪፖርቶችን የሚሰበስብ ይሆናል። ኅብረቱ በመስከረም 20/2014 ዓም በሚካሄደው ምርጫ ላይ ዜጎች በሰላማዊ መንገድ እንዲሳተፉ ያበረታታል።